## ነፃ የኖርዊጂያን ቋዋንቋ እና የኖርዊጂያን ማህበረሰብ መሰረታዊ እውቀት አስጨባጭ ስልጠና

በኖርዌ የሏት ወይም የተሰጦት የመኖሪያ ፈቃድ ነፃ የኖርዊጂያን ቋዋንቋ እና የኖርዊጂያን ማህበረሰብ መሰረታዊ እውቀትን አስጨባጭ ስልጠና የማግኘት ወይም የመካፈል መብትን ይሰጥዎታል ።
በሕዝብ መመዝገብያ በተመዘጋቡበት አውራጃ ወይንም ኮሚውን በሚገኘው የጓልማሶች ወይም የአዋቂዎች የትምህርት መስጫ ማእከል በተቻለ ፍጥነት ይህን ስልጠና ለማግኘት ወይም ለመካፈል እንዲችሉ ማመልከት ያስፈልግዓታል ።
ስልጠናውን በነፃ የማግኘት መብትዋ የሚጸናበት የተቆረጠልት የቀን ግድብ መቆጠር የሚጀምረው የመኖሪያ ፈቃድ በኖርዌ ውስጥ ለመኖር ፍቃድ ከአገኙበት ቅን ጀምሮ ወይም ወደ ኖርዌ ፈቃድ ይዘው ከገቡበት ቀን ጀምሮ ይሆናል። መለስተኛ ሁለተኛ ደረጃን ሳያጠናቅቁ ከሆነ ወደ ኖርዌ የመጡት የተቆረጠለት ቀን በሶስት ዓመታት በኖርዊ ቆይታዎት ውስጥ ይሆኖል። የመለስተኛ ሁለተኛ ደረጃውን አጠናቃው ለመጡት ግን ስልጠናውን ኖርዌ ከገቡበት በ18 ወራት ውስጥ ይሆናል ።

## የኖርዊጂያን ቋዋንቋ እና የኖርዊጅያን ማህበረሰብ አሰጨባጭ ስልጠና የመከታተል ግዴታ

የኖርዌ አገር ዜግነትን ለማግኘትም ሆነ በኖርዌ ቋሚ የሆነ የመኖሪያ ፈቃድን ለማግኘት የኖርዊጂያን ቋዋንቋ እና የኖርዊጂያን የማህበረሰብ መሰረታዊ እውቀት አሰጨባጭ ስልጠናን የማጠናቀቅ ግዴታ ይኖርቧታል።
የኖዊጂያን ቋዋንቋ ወይም የሳሚዎች ቋዋንቋ በቂ ችሎታ ያለዎት መሆኑን የሚያረጋግጥ ሰነድ ማቅረብ የሚችሉ ከሆነ ወይም የተለየ የጤና እክል ወይም ሌላ ከበድ ያለ ስልጠናውን ከመውሰድ ነጻ ሊያደርገዎት የሚያስችል ኣሳማኝና በቂ ምክንያት ካለዎት ብቻ ይሆናል።

## የኖርዊጂያን ቋዋንቋ እና የኖርዊጂያን ማህበረሰብ አሰጨባጭ ስልጠና የመከታተል መብትና ግዴታ

መብትና ግዴታው የሚኖርዎት የመጨራሻ ዝቅተኛ የኖርዊጂያን ቋንቋ ደረጃ እስኪያጠናቅቁ ድረስ ይሖናል።
ይኽ ደረጃ የሚወሰነው በአውራጃው ወይም በኮሚውኑ ይሆናል ። ይኽንን የመጨራሻ ዝቅተኛ ቋንቋ ደረጃ እስኪያጠናቅቁ ድረስ ስልጠናው በነጻ ይሆናል ። ይኽንን ስልጠና ከመውሰድ ፈቃድ ከአገኙ ግን ስለጠናውን ለመውሰድ ወይም ለመካፈል የተቆረጠው ቀን ይራዘማል ።

## በተግባር ስለሚፈጸሙ ነገሮች መግለጫ

በተጨማሪም ማንኛውም ጥያቄ ካለዎት እንደዚሁም መብትን ወይም የጊዜ ገደቧችን የሚመለከት ጥያቂዎች ከአሎዎት ከዚሁ የጎልማሶች(አዋቂዋች) ማሰልጠኛ ማእከልን ማግኘት ይቻላል።

እንደዚሁም በተጨማሪ መግለጫዋችን ከwww.imdi.no እና ከwww.udi.no ከሚሊት ድኽረ ገጾች ማግኘት ይቻላል።